በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

የሥልጠና ርእስ፡ ሕገ ቤተክርስቲያን

***ሙሉ ሰነዱ በቅዱስ ሲኖዶስ በ **1991** ዓ.ም. የጸደቀው ሕገ ቤተክርስቲያን ነው

አዳዲስ አባላትንና ተተኪ አመራር አባላትን ለማፍራት ለሚሰጠው ሥልጠና የተዘጋጀ

የማሠልጠኛ ጽሑፍ

በሀገር ውስጥ ማእከላትና ግቢ ጉባኤያት ማ/ማ ዋና ክፍል

የተዘጋጀ

2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

<u>ሕገ ቤተክርስቲያን</u>

<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ሕግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የ 1991 ዓ.ም ሕገ ቤተክርስቲያን ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ሕግ ውስጥ፣

1. “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን” ማለት ክርስቶስን በተዋሕዶ አንድ አካል፣ እና አንድ ባሕርይ፣ ብላ የምታምን ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት፣ ታሪካዊት ቤተክርስቲያን ናት።
2. “ቅዱስ ሲኖዶስ” ማለት ፓትሪያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የሚያደርጉት ዓቢይ ጉባኤ ነው።
3. “ፓትሪያርክ” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ርዕሰ አበው አበ ብዙኃን ማለት ነው።
4. “ሊቀ ጳጳስ” ማለት በኤጲስ ቆጶስነት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ሊቀ ጳጳስ ተብሎ የሚሰየም የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።
5. “ኤጲስ ቆጶስ” ማለት በድንግልና መንኩሶ ቤተ ክርስቲያንን በዲቁናና በቅስና እንዲሁም በቁምስና ሲያገለግል ከቆየ በኋላ የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ የተቀበለ የቤተክርስቲያን ጠባቂ ወይም ኖላዊ ማለት ነው።
6. “ቋሚ ሲኖዶስ” ማለት

   ሀ/ ቅዱስ ፓትሪያርክ

   ለ/ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ

   ሐ/ የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ

   መ/ ከሲኖዶስ አባላት መካከል አራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት በአባልነት የሚገኙበት ጉባኤ ነው።
7. “የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ” ማለት የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ነው።
8. “ጠቅላይ ጽ/ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ (ቤተ ክህነት) ጽ/ቤት ነው።
9. “ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተመርጦ በፓትሪያርኩ የተሠየመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ (ቤተ ክህነት) ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ነው።
10. “አስተዳደር” ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከአጥቢያ እስከ ሀገረ ስብከት ከዚያም እስክ ጠቅላይ (ቤተ ክህነት) ጽ/ቤት ያለውንና የድርጅቶችን አመራር የሚያጠቃልል የአስተዳደር ሥራ ነው።
11. “የአስተዳደር ጉባኤ” ማለት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሚመራ የመምሪያና የድርጅት ኃላፊዎች የሚገኙበት ስብሰባ ነው።
12. “መምሪያ” ማለት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሚገኝ ዓቢይ የሥራ ዘርፍ ነው።

13. “ሀገረ ስብከት” ማለት የሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ነው።
14. “መሥሪያ ቤት” ማለት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲሁም በየደረጃው የተቋቋሙት የድርጅቶች ጽ/ቤት ነው።
15. “ሠራተኛ” ማለት በቤተ ክርስቲያኒቱ መ/ቤቶች በቋሚነት ወይም በኮንትራት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሕጋዊ ሰውነት</u>

1. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምላክ የመሠረታት በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ስለሆነች ራሷን የመምራትና የማስተዳደር መብት አላት፣
2. በሀገሪቱ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 398 እና 399 በተደነገገው መሠት

   ሀ/ በመሥሪያ ቤቶቿ አማካኝነት በአስተዳደር ሕጐች የተፈቀዱትን መብቶች ሁሉ ልታገኝና ልትሠራባቸው

   ለ/ ውል ለመዋዋል፣ ለመክሰስና ለመከሰስ ባለንብረት ለመሆን ለመግዛት፣ ለመሸጥና ውርስ ለመቀበል ትችላለች።
3. ቤተክርስቲያኒቱ በምታስተዳድራቸው ካህናትና ምእመናን ላይ ባላት የዳኝነት ሥልጣን መሠረት፣

   ሀ/ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ውስጥ ለሚፈጸሙ የሥራ ጉድለቶች በቤተክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መሠረት የመቆጣጠር፣ የመቅጣት፣ የማረም፣ ከሥራ የማስወገድ በጡረታ የማግለል ወዘተ.... መብት አላት።

   ለ/ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዳኝነት እንደክሱ አቀራረብ እየተመዘነ የሚታየው፣

   ለ.1. በዲሲፕሊን ጉባኤ /በሥነ ሥርዓት ጉባኤ/

   ለ.2. በመንፈሳዊ ፍ/ቤት

   ለ.3. በአስተዳደር ጉባኤ

   ለ.4. በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ነው። በቅ/ሲኖዶስ የሚወሰኑ ውሳኔዎችም የመጨረሻ ይሆናሉ

   ሐ/ የእያንዳንዱም የዳኝነት ሥልጣን ከቤተ ክርስቲያኒቱ በሚወጡ ሕጎችና ደንቦች ይወሰናል።

   መ/ ካህናት፣ ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃነ ጳጳሳት መንፈሳዊ ሥራቸውን (አገልግሎታቸውን)

   በሚመለከት ጉዳይ ሲከሰሱ በቤተ ክርስቲያን ሕግና የዳኝነት ሥርዓት ይታያል እንጂ

   በሥጋዊ ዳኝነት አይከሰሱም።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣን መዋቅር</u>

1. ቅዱስ ሲኖዶስ
2. ፓትሪያርክ

3. ቋሚ ሲኖዶስ
4. የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት
5. የሀገረ ስብከት ክህነት
6. የወረዳ ቤተ ክህነት
7. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ</u>

<u>የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና /የበላይነት/</u>

1. በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅ/ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን ባለቤት ነው።
2. ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን መዋቅር ሁሉ የበላይ አካል ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ሕጐችን ፣ ልዩ ልዩ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣትና የዳኝነት ሥልጣን አለው።

<u>የቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማ</u>

1. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ፣
2. ሃይማኖትና ቀኖና ቤተክርስቲያን እንዳይፋለስ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፣
3. ጥንታዊውን የቤተክርስቲያን ትምህርት ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣
4. ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ለማጠናከር፣
5. ወጣቶች ከአበው የተቀበሉትን ሃይማኖትና ሥርዓት ጠብቀው በትምህርትና በሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ሰንበት ት/ቤትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት፣
6. የሰው ዘር ሁሉ ከርሃብ፣ ከእርዛት፣ ከበሽታና ከድንቁርና ተላቆ በሰላምና በአንድነት በመተሳሰብና በመረዳዳት በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖር ማስተማርና መጸለይ፣

<u>የቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተክርስቲያን በበላይነት ይመራል፣ ይጠበቃል።
2. ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት ሕጐችን ፣ ደንቦችንና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ይወስናል።
3. የቤተ ክርስቲያኒቱን አጠቃላይ የምጣኔ ሀብትና የሙዓለንዋይ መመሪያዎችን /ፖሊሲዎችን/ ይወስናል።
4. ዓመታዊውን በጀት ያጸድቃል ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል።
5. የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደራዋ መዋቅር እንዲሁም የጽሕፈት ቤቶችን ደረጃና ተጠሪነት ያዘጋጃል።

6. የቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደርና አገልግሎት በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት እንዲመራ ያደርጋል።
7. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት በአገር ውስጥና በውጭ አገር እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ት/ቤቶችንም ያቋቁማል።
8. የክርስቶስን ወንጌለ መንግሥትና ቀኖና ቤተክርስቲያንን ያስተምራል ያስፋፋል።
9. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር አዲስ የሀገረ ስብከት ጽ/ቤትና መንበረ ጵጵስና እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል።
10. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት ያስፋፋል ያጠነክራል።
11. በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከትና አጥቢያ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ሊመደቡና እንደዚሁም በአገር ውስጥ የሚሰጠውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት ተምረው የውጭውን ትምህርት መማር የሚችሉ ካህናትን እየመረጠ እንዲላኩ ያደርጋል።
12. ማንኛውም ሰው ቤተ ክርስቲያንቱን ወክሎ ለሥራም ሆነ ለጉብኝት ወደ ውጭ አገር በሚላክበት ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ እየፈቀደ ነው።
13. ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ በምልዓተ ጉባኤ እየወሰነ በቤተክርስቲያኒቱ ሕግ መሠረት እንዲመረጡና እንዲሾሙ ያደርጋል። እንዲሁም ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን በየሀገረ ስብከቱና በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ይመድባል በበቂ ምክንያት ያዘዋውራል።
14. በቋሚ ሲኖዶስ የሚያገለግሉ ጳጳሳትን በየሦስት ወሩ እየመደበ እንዲሠሩ ያደርጋል።
15. በኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚመደቡትን
    ሀ/ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፈሐፊ
    ለ/ የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ
    ሐ/ የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤቱ ም/ሥራ አስኪያጅ
    መ/ የልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር
    ሠ/ የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
    ረ/ የልዩ ልዩ ሥራ ዘርፎች ቦርድ አባላት እየመረጠ እንዲሾሙ ያደርጋል።
16. ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ያጸድቃል እንደአስፈላጊነቱም ያሻሽላል።
17. ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ለጥፋተኞችና ለበደለኞችም ምሕረትና ይቅርታ የመስጠት ሥልጣን የቅዱስ ሲኖዶስ ነው።
18. በዚህ ሕግ ባልተካተቱ በማናቸውም በቤተክርስቲያኒቱ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ቅዱስ ሲኖዶስ የመወሰን ሥልጣን አለው።

የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት

1. በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት ፓትሪያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አህጉረ ስበከትና በልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የተሾሙ ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ናቸው።
2. ከፓትሪያርኩ ጀምሮ እያንዳንዱ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስና ኤጲስ ቆጶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው።
3. የቅዱስ ሲኖዶስ አባልነት ዕድሜ ልክ ይሆናል።
4. አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተክርስቲያንን የሚያፋልስ ሆኖ ከተገኘ ከአባልነቱ ይሠረዛል፤ይህም የሚሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነው።
5. በሃይማኖትም ሆነ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተከሰሰ የሲኖዶስ አባል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ቀርቦ ራሱን የመከላከል መብቱ የተጠበቀ ነው።
6. አንድ የሲኖዶስ አባል ስለራሱ ጉዳይ በሚታይበት ስብሰባ ላይ በአባልነት መገኘት አይችልም።

የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ

1. የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፓትሪያርኩ ሰብሳቢነት ይመራል። ፓትሪያርኩ በልዩ ልዩ ምክንያት ጉባኤውን መምራት ባይችል ከአባላቱ መካከል እሱ የሹመት ቅድምና ያለውን አባት በመወከል ስበሰባው ሊመራ ይችላል።
2. ከዚህ በታች ከተመዘገቡት በሶስት ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ፓትሪያርኩ ርዕሰ መንበር ያልሆነበት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ሊካሄድ አይችልም።

   ሀ/ ፓትሪያርኩ በዕርግናና በጤና ጉድለት ምክንያት ጉባኤውን የሚመራ አባት መወከል ካልቻለ፣

   ለ/ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ቀኖና በተመለከተ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ እንዲደረግ የሲኖዶሱ አባላት ሲጠይቁት ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ፣

   ሐ/ ስብሰባው ፓትሪያርኩን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ በፍትሐ መንፈሳዊ መሠረት ይፈጽማል።
3. ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፓትሪያርኩ ጉባኤውን መምራት ካልቻለ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በተመረጠ የሹመት ቅድምና በአለው አንድ አባት ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል።

የቅዱስ ሲኖዶስ የስብሰባ ሥርዓት

1. ፍትሕ መንፈሳዊ በአምስተኛው አንቀጽ ቁጥር 164 በሚያዝዘው ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል። የስብሰባውም ጊዜ፣

   ሀ/ የመጀመሪያው ጉባኤ በየዓመቱ ጥቅምት 12 ቀን

   ለ/ የሁለተኛው ጉባኤ ትንሣኤ በዋለ በሃያ አምስተኛው ቀን /በርክበ ክህናት/ የሚካሄደው ነው።

2. አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም

   ሀ/ ቅዱስ ፓትሪያርኩ ወይም ቋሚ ሲኖዶስ በሚያደርጉት ጥሪ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሊካሄድ ይችላል።

   ለ/ ከጠቅላላው አባላት ከሦስት ሁለት እጅ የሚሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ምልዓተ ጉባኤ እንዲደረግ በጠየቁ ጊዜም ጥሪ ሊደረግና ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል።

3. የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የሚባለው ከዓቅም በላይ የሆነ ዕክል ካላጋጠመ በቀር መላው አባላት የተገኙበት ጉባኤ ሲሆን ነው።

4. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሕመምና በልዩ ልዩ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት አንዳንድ አባላት ባይገኙ፣

   ሀ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተክርስቲያንን በሚመለከት ጉዳይ ከጠቅላላው አባላት ከአራት ሦስት እጅ የተገኙ ከሆነ፣

   ለ/ አስተዳደርን በሚመለከት ጉዳይ ከጠቅላላው አባላት ከሦስት ሁለት እጅ የተገኙ ከሆነ ነው።

5. ቅዱስ ሲኖዶስ በማናቸውም ስብሰባ ላይ ውሣኔዎችን ሲያሳልፍ፣

   ሀ/ አስተዳደርን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ከተገኙት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በሆነ ድምፅ የተደገፈው ሐሳብ ያልፋል።

   ለ/ አንድን ጉዳይ ለመወሰን የአባላቱ ድምፅ እኩል በኩል ከሆነ ቅዱስ ፓትሪያርኩ ያለበት ያልፋል።

   ሐ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተክርስቲያንን የሚመለከት ከሆነ በሙሉ ድምፅ ያልፋል።

<u>የቋሚ ሲኖዶስ አባላትና ስብሰባ</u>

1. ቋሚ ሲኖዶስ በዚሁ ሕገ ቤተ ክርስቲያን በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 14 መሠረት በየሦስት ወሩ አባላቱ እየተተኩ ሥራው በቋሚነት የሚሠራበት፣ ሕግን የመተርጐምና የማስፈጸም መብት ያለው አካል ነው።

2. የቋሚ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ፓትሪያርክ ነው፤ ፓትሪያርኩ በማይኖርበት ጊዜ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ተወክሎ ሰብሳቢ ይሆናል። አባላቱም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተመረጡ አራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት ይሆናሉ።

3. የቋሚ ሲኖዶስ ስብሰባ በየዕለቱ ይሆናል።

4. ቋሚ ሲኖዶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

የቋሚ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር

1. በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ እየተወሰኑ የሚተላለፉ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ተግባራዊ መሆናቸውን በየዕለቱ ይከታተላል።
2. የቅዱስ ሲኖዶስን ምልዓተ ጉባኤ የማያስፈልጉ አስተዳደር ነክ በሆነ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ይወስናል።
3. ከየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት የሚቀርበው የሥራ ሪፖርት ተቀነባብሮ ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲቀርብ ያደርጋል።
4. ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርገው ጉባኤ የሚነጋገርባቸውን አጀንዳዎች ያዘጋጃል።
5. አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲደረግ ይወስናል።
6. ዓመታዊ በጀት ተጠንቶና ተዘጋጅቶ በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት እንዲጸድቅ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ያቀርባል።
7. ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኒቱ ገቢና ወጭ በበጀት መሠረት መሠራቱን ይቆጣጠራል።

የኢትዮጵያ ፓትርያርክ

ስለ ቅዱስ ፓትርያርክ ምርጫ

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የቤተክርስቲያኒቱ ሕግና ቀኖና በሚፈቅደው መሠረት ተመርጦ ይሾማል።
2. ቅዱስ ሲኖዶስ ስለፓትርያርክ ምርጫ በሚወስነው ቁጥር መሠረት አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፣
3. ለፓትርያርክነት የሚመረጡት እጩዎች ከሊቃነ ጳጳሳትና ከኤጲስ ቆጶሳት መካከል ሲሆን ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ ከአምስት ያልበለጡ ይሆናል።
4. አስመራጭ ኮሚቴው እጩዎችን ጠቁሞ ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፣ በቤተክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መሠረት ምርጫው እንዲካሄድ ይደርጋል።
5. መራጮች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በሙሉ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የየመምሪያና ድርጅት ኃላፊዎች፣ የጥንታውያን ገዳማት አበምኔቶች፣ የአድባራት አስተዳዳሪዎች ከየሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤያት በዕድሜ ከ 30 ያላነሱ የካህናትና የምእመናን ተወካዮች እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ 22 እስከ 30 ዓመት የሆኑ የሰንበት

ት/ቤት ተወካዮች ሲሆኑ በጠቅላላው በሰበካ ጉባኤው የሚወክሉት ከአንድ ሀገረ ስብከት አሥራ ሁለት ሆነው በሥጋወደሙ የተወሰኑ በሕገ ቤተክርስቲያን የጸኑ መሆን አለባቸው።

6. የምርጫው አፈጻጸም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።
7. የተመረጠው ፓትርያርክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቀኖናዋን ሊጠብቅና አድልዎ በሌለው መልኩ ቤተክርስቲያኒቱን ሊያስተዳድር ቃለ መሐላ ይፈጽማል።
8. ከዚህ በላይ የተደገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፓትርያርክ ምርጫ ቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ ያወጣል።

<u>የፓትርያርኩ የማዕረግ ስምና መንበር</u>

1. ፓትርያርኩ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ እገሌ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ይባላል፤ ስሙም በመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በጸሎት ይጠራል።
2. ፓትርያርኩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ አባት ነው።
3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ መንበር በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ነው።

<u>የፓትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ፓትርያርኩ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተክርስቲያንን ይጠበቃል ያስጠበቃል።
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፓትርያርኩ የቅዱስ ሲኖዶስን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት ይመራል።
3. ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 እና በዚሁ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 13 መሠረት ፓትርያርኩ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋር ሆኖ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾማል፣ እንዲሁም ቅ/ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሲስማማበት ለብፁዓን ጳጳሳት የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ ይሰጣል።
4. በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 15 መሠረት የተመረጡትን የሥራ ኃላፊዎች ይሾማል፣በቀደምትነት በታሪክ የታወቁትን የታላላቅ ገዳማት አበምኔቶችና የከፍተኛ አድባራት አስተዳዳሪዎች በየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት እየተመረጡ ሲቀርቡለት የማዕረግ ስም እየሰጠ ይሾማል።
5. ስለ ቤተክርስቲያን ጉዳይ የመንግሥትን ፈቃድ ማግኘት በሚያስፈልግበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ በተግባር ላይ ያውላል።
6. ቅዱስ ፓትሪያርኩ በዓበይት ጉዳዮች ላይ ሁሉ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ ይሠራል።

7. በቅዱስ ሲኖዶስ የወጡ ሕጐች፣ የተላለፉ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ሁሉ በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
8. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡትን ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በፊርማው ያስተላልፋል።
9. ከመንግሥታውያንም ሆነ መንግሥታውያን ካልሆኑ መ/ቤቶች ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚቀርቡ ደብዳቤዎች ወይም አቤቱታዎችን ደረጃቸውን ጠብቀው በሕግ መሠረት ይፈጸሙ ዘንድ ለጠቅላይ ጽ/ቤት ያስተልልፋል።
10. በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን አህጉረ ስብከት ለማገልገል ወይም የነፃ ትምህርት ለመማር የሚላኩ ካህናት በዚሁ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ተመርጠው ሲቀርቡ እንዲላኩ ያደርጋል።
11. ከውጭ የሚመጡትን እንግዶች በውጭ ጉዳይ ኃላፊ አቅራቢነት እየተቀበለ ያነጋግራል።
12. ፓትርያርኩ በውጭ አገር በሚደረግ በማናቸውም ስብሰባ ላይ ለመገኘትና ጉብኝት ለማካሄድ በሚያስፈልግ ጊዜ ስለተልዕኮው ጉዳይ አስቀድሞ በቅዱስ ሲኖዶስና በቋሚ ሲኖዶስ ያስወስናል።

<u>የፓትርያርኩ ከማዕረግ መውረድ</u>

1. ፓትርያርኩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ላይ ከተሾመ በኋላ የተቀበለውን ኃላፊነት በመዘንጋት።

   ሀ/ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፣ቀኖና ቤተክርስቲያንን የማይጠብቅ ቤተክርስቲያንን የሚያስነቅፍ ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ፣

   ለ/ በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 172 እስክ 208 በተደነገገው መሠረት በደለኛ መሆኑ ከታመነበት፣

   ሐ/ በቃሉ የማይገኝና በዚህ ሕግ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀፍ ድንጋጌ መሠረት በተሾመበት ቀን የፈጸመውን ቃለ መሐላ ያልጠበቀ በአጠቃላይ ታማኝነቱ መንፈሳዊ አባትነቱ በካህናትና በምእመናን ዘንድ ተቀባይነትን ያጣ ሆኖ ቤተክርስቲያኒቱን የሚያስነቅፍ መሆኑ በትክክል ከተረጋገጠ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከሥልጣኑ ይወርዳል፤በምትኩም ሌላ ፓትርያርክ ተመርጦ ይሾማል።
2. ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት ከሥልጣኑ የተገለለ ፓትርያርክ በቀኖና ተወስኖ በገዳም ይቀመጣል።
3. ከሥልጣን የተገለለው ፓትርያርክ በገዳም አልቀመጥም በቀኖናም አልወሰንም በማለት እምቢተኛ ከሆነ ተወግዞ ከቤተክርስቲያን አንድነት ይለያል።
4. ፓትርያርኩ መንፈሳዊ ሥራውን በማካሄድ ላይ እያለ እሥራትና ግዞት ቢደርስበት ቤተክርስቲያኒቲ በቅዱስ ሲኖዶስ ትመራለች እንጂ ሌላ ፓትርያርክ አይሾምም።
5. ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁሉ ፍትሕ መንፈሳዊ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል።

ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ

1. ፓትርያርኩ በሞት ሲለይ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 16 መሠረት ከሥልጣኑ ሲወርድ ቅዱስ ሲኖዶስ በሹመት ቀደምትነት ካላቸው ሊቃነ ጳጳሳት መካከል በዕለቱ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ መርጦ ይሾማል። የተተኪው ፓትርያርክ ምርጫም ይካሄዳል።
2. የተተኪው ፓትርያርክ ምርጫ አፈጻጸም እንደጊዜውና እንደሥራው ሁኔታ እየታየ ከ 40 እስከ 80 ቀን ባለው ጊዜ ይሆናል።
3. የዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ተግባር፣

   ሀ/ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ጊዜያዊ ጉዳዮችን ከቋሚ ሲኖዶስ ጋር እየመከረ ያከናውናል።

   ለ/ በፓትርያርኩ ምርጫ ጊዜም የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ሆኖ ምርጫውን ያስፈጽማል፤ እርሱ ግን ከምርጫው አይገባም።

ስለ ኤጲስ ቆጶሳት

የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠት የኤጲስ ቆጶስ ምርጫ የሚፈጸመው፣

1. ኤጲስ ቆጶስ እንዲሾም አስፈላጊ መሆኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲታመንበትና ሲወሰን፣
2. በሥርዓተ ምንኩስና በድንግልና መንኩሰው ቤተ ክርስቲያንን ከሚያገለግሉና ለኤጲስ ቆጶስነት ብቁ ከሆኑት ቆሞሳት መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ዕጩ ሆኖ ሲቀርብ፣
3. ለኤጲስ ቆጶስነት ዕጩ ሆኖ የሚቀርበው ቆሞስ ከዚህ የሚከተለውን መመዘኛ የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ነው።

   ሀ/ ቆሞሱ በመነኮሰበት ገዳም ከሦስት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ያገለገለ፣

   ለ/ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ባይሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታይ ሆኖ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ፣

   ሐ/ በትምህርት ሃይማኖት /በነገረ መለኮት/ በቂ ችሎታ ያለውና ቀኖና ቤተክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ፣

   መ/ በግብረ ገብነቱ የተመሰገነ፣

   ሠ/ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ፅኑዕ የሆነ፣

   ረ/ ሙሉ አካል ያለው ፣ ጤንነቱ የተሟላ፣

   ሰ/ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በመፈጸም የአስተዳደር ልምድ ያለው፣

ሽ/ ዕድሜው ከ 45 እስከ 60 ዓመት የሆነው፣

4. ኤጲስ ቆጶስ በሚመረጥበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰየም አስመራጭ ኮሚቴ ተጠቁሞ የሚቀርብ ይሆናል።

<u>የኤጲስ ቆጶስ ሹመትና የማዕረግ ስም</u>

1. በዚህ ሕገ ቤተክርስቲያን አንቀጽ 18 በተደነገገው መሠረት ቆሞሱ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በዕጩነት ተመርጠው ከቀረቡት መካከል ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 90-95 በሚያዝዘው መሠረት በድምጽ ብልጫ ይመረጣል፤ተወዳዳሪዎቹ ያገኙት ድምፅ እኩል ከሆነ እጣ የወጣለት ቆሞስ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ይሾማል።
2. ኤጲስ ቆጶሱ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ብፁዕ አቡነ እገሌ ተብሎ ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው የኤጲስ ቆጶስነት ስም ይሠየማል። ስሙም በሀገረ ስብከቱ ዘወትር በጸሎት ይጠራል።
3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ቦታ ሁሉ ኤጲስ ቆጶሱ በአገልግሎት ጊዜ ከደረሰ በተገኘበት ጸሎት ላይ ብቻ ስሙ ይጠራል።
4. ኤጲስ ቆጶሱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና መሠረት ተቀብቶ የሚሾመው በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 13 ድንጋጌ መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው ሀገረ ስብከት ወይም አስፈላጊ በሆነ የሥራ ቦታ ነው።

<u>የኤጲስ ቆጶስ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ኤጲስ ቆጶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለፓትርያርኩ ነው፣ ካህናትንና ምእመናንን የመምራት፣የማስተማር፣ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን የመፈጸምና የማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን አለው።
2. በሀገረ ስብከት የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ በዚህ ሕግ አንቀጽ 37(1-10) ለሊቀ ጳጳስ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ለኤጲስ ቆጶሱም ይሆናል።
3. ኤጲስ ቆጶሱ በተሾመበት ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ካለ ኤጲስ ቆጶሱ ተጠሪነቱ በሀገረ ስብከቱ ላለው ሊቀ ጳጳስና ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ ከሊቀ ጳጳሱ ጋር እየተመካከረና መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል።

<u>የኤጲስ ቆጶስ ግዴታና ኃላፊነት</u>

1. ኤጲስ ቆጶሱ በተሾመበት ሀገረ ስብከት ይኖራል።
2. በፓትርያርኩ ፈቃድ ወይም በሥራ ምክንያት ወይም በሕመም ምክንያት ካልሆነ በቀር ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ከአሥራ አምስት ቀን የበለጠ መቆየት አይችልም።

3. ሊቀ ጳጳሱ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ በፍትሐ መንፈሳዊ በአንቀጽ 5 ቁጥር 156-161 በተደነገገው መሠረት ሳይፈቀድለት ወይም ሳይጠይቅ በሌላው ሀገረ ስብከት ጉብኙ ክህነት መስጠት፣ መዳኘት ፣ አዲስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት መባረክና የመሳሰሉትን ዓበይት ተግባራት መፈጸም አይችልም፤ ይህን አድርጐ ቢገኝ የተጠቀሰው አንቀጽ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል።
4. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንዱ ሀገረ ስብከት ወደ ሌላው ሄደው ማዕረግ ዲቁናና ቅስና ለመቀበል የሚጠይቁ ካሉ የትምህርት ችሎታቸውንና ከሀገረ ስብከቱ የተሰጣቸውን ማስረጃ እያየ ማዕረጉን ሊሰጣቸው ይችላል።
5. ኤጲስ ቆጶሱ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ጉባኤ የሥራ ሪፖርት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ያቀርባል፤ በምልዓተ ጉባኤው ስብሰባ ላይም ይገኛል።
6. ያለበቂ ምክንያትና ያለቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የኤጲስ ቆጶስነቱን ማዕረግ በፈቃዱ እንዲተው አይፈቀድለትም።
7. ኤጲስ ቆጶሱ በጊዜ ዕረፍቱ የኤጲስ ቆጶስነት ተልዕኮውን ሲፈጽም ከኖረበት ሀገረስበከት ይቀበራል።

ስለ ኤጲስ ቆጶስ ዝውውር

1. በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አምስት በቁጥር 158 በተወሰነው መሠረት አንድ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመበት ሀገረ ስብከት ሊዛወር አይችልም።
2. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ/ በዕድገት ወይም በሌላ ሥራ ምክንያት ወደ ሌላ እንዲዛወር አስፈላጊ ከሆነ፣

   ለ/ ኤጲስ ቆጶሱ በተመደበበት ቦታ ለመቆየት አስቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ በቅዱስ ሲኖዶስ ተጠንቶ በውሳኔ ሊዛወር ይችላል።

3. በተመደበበት ሀገረ ስብከት ወይም የሥራ ቦታ መቆየት አይችልም ተብሎ የተወሰነበት ወይም የተወሰነለት ኤጲስ ቆጶስም በሌላ ቦታ ሊመደብ የሚችለው በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ ነው።

የኤጲስ ቆጶስ ከማዕረግ መውረድ

አንድ ኤጲስ ቆጶስ ከማዕረጉ የሚወርደው በዚህ ሕግ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4-5 እና አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ-ሐ/ ድንጋጌ መሠረት ነው።

ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ

የዋና ጸሐፊው ምርጫ

1. በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በሚሠየም አሥመራጭ ኮሚቴ አቅራቢነት ከሲኖዶስ አባላት መካከል ሦስት ተወዳዳሪዎች ቀርበው በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ይመረጣል።
2. ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊነት የተመረጠው ሊቀ ጳጳስ ፣ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ በቅዱስ ፓትርያርኩ ይሾማል።
3. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የሲኖዶስ አባልና ጸሐፊ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ይሁንና የዕለት ከዕለት ሥራውን ከቅዱስ ፓትርያርኩ መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል።
4. የሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለአንድ የምርጫ ዘመን እንደገና ሊመረጥ ይችላል።
5. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመረጠው ጸሐፊ የጸሐፊነቱን ሥራ ለመቀጠል የማያስችለው በቂ ምክንያት ባጋጠመ ጊዜ ባይደርስም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በሌላ ሊተካ ይችላል።

የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ ሥልጣንና ተግባር

1. ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርገው ጉባኤ ላይ ሁሉ በቋሚ ሲኖዶስ የሚዘጋጀውን ርዕሰ ጉዳይ /አጀንዳ/ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ያቀርባል።
2. በየጊዜው በሚያደርገው በቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ እየተገኘ ቃለ ጉባኤ ይይዛል።
3. ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠውን ውሳኔና ትእዛዝ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያስተልልፋል።
4. የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች ሁሉ በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከተተላል፣ይቆጣጠራል።
5. የሚተላለፈው የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔና ትእዛዝ በሥራ ላይ ካልዋለ ምክንያቱን በመግለጽ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሪፖርት ያቀርባል።
6. ጸሐፊው በቅዱስ ሲኖዶስ ያልተወሰነ ጉዳይ ማስተላለፍ አይችልም።

7. አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም በዚህ ሕግ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ መሠረት ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ ቋሚ ሲኖዶስ በወሰን ጊዜ ጸሐፊው ከፓትርያርኩ ጋር እየተመካከረ የሲኖዶሱን አባላት በጽሁፍ ይጠራል።
8. በጠቅላይ ጽ/ቤት ውስጥ ዋና ጸሐፊው አንድ ጽ/ቤት ይኖረዋል፤ የሲኖዶሱን ማኅተምና ልዩ ልዩ ሰነዶችን ተረክቦ በጥንቃቄ ይይዛል።

<u>የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ</u>

1. የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ይመረጣል።
2. የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ችሎታና ሥልጣነ ክህነት ያለው ይሆናል።
3. ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ነው።

<u>የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ተግባር</u>

1. የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ከዋና ጸሐፊው መመሪያ እየተቀበለ ለዋና ጸሐፊው ረዳት ሆኖ ይሠራል።
2. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ነው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት</u>

<u>የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት መዋቅር</u>

1. ጠቅላይ ጽ/ቤቱ የሥራ አስፈጻሚነትና የአስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ከፍተኛ አካል ነው።
2. በቅዱስ ሲኖዶስ የተሠየመ አንድ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅና አንድ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ይኖሩታል።
3. የመምሪያ ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበትና በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሚመራ አንድ አስተዳደር ጉባኤ ይኖረዋል።
4. በጠቅላይ ጽ/ቤቱ ሥር ኮሚሽን፣መምሪያዎች፣ ድርጅቶችና ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ይኖራሉ። እነሱም

ሀ/ መምሪያዎችና የአገልግሎት የሥራ ዘርፎች፣

1. ሊቃውንተ ጉባኤ
2. ስብከተ ወንጌል መምሪያ
3. ትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያዎች
4. መንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ

5. ሰበካ ጉባኤ መምሪያ
6. ሰንበት ት/ቤት ማደራጃ መምሪያ
7. መንፈሳዊ ፍርድ ቤት
8. ሕግ አገልግሎት
9. የሕግ አማካሪ
10. አስተዳደር መምሪያ
11. ገንዘብና በጀት መምሪያ
12. ቁጥጥር አገልግሎት
13. የውጭ ጉዳይ መምሪያ
14. የቅርሳቅርስ ጉዳይ መምሪያ
15. እቅድና ልማት መምሪያ

ለ/ ኮሚሽንና በቦርድ የሚተዳደሩ፣

1. ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
2. የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ
3. ቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደር

ሐ/ ድርጅቶች

1. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
2. ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
3. አልባሳት ማዘጋጃና ምርት ስርጭት
4. የቁልቢ ቅ/ገብርኤል ገዳም ንዋየ ቅድሳት ማደራጃ
5. የጮፋ ጥበበ እድ ማሠልጠኛ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ

1. በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሠየም አስመራጭ ኮሚቴ አቅራቢነት ከሲኖዶስ አባላት መካከል ሦስት ዕጩዎች ተወዳድረው በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የተመረጠው ሊቀ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በቅዱስ ፓትርያርኩ ይሾማል።

2. ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት የተመረጠው ሥራ አስኪያጅ ሹመት ጉዳይ ለሚመለከታቸው ሁሉ በቅዱስ ፓትርያርክ ፊርማ ይገለጻል።
3. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለቅዱስ ፓትርያርኩ ነው።
4. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ነው አስፈላጊም ሆኖ ከተገኘ ለአንድ የምርጫ ዘመን እንደገና ሊመረጥ ይችላል።
5. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥራውን ለመቀጠል የማያስችል ምክንያት ካጋጠመው የአገልግሎቱ ዘመን ሳይፈጸም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ በሌላ ሊተካ ይችላል።

<u>የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በየጊዜው የሚወስናቸውን ጉዳዮችና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ መ/ቤቶችም ሆነ ከየሀገረ ስብከቱ የሚቀርቡትን ጥያቄዎችን ሁሉ በሕጉ መሠረት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል።
2. የዋናውን መ/ቤት፣ ቦርዶችን ፣ኮሚሽኖችን፣ ድርጅቶችንና መምሪያዎችን እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥር የሚገኙትን የሥራ ዘርፎች ሁሉ ያስተዳድራል፣ ይመራል።
3. ከቤተ ክርስቲያኒቱ አቅዋም ጋር የሚስማሙ ሥራዎችን በማካሄድና የገንዘብ ምንጭ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት የሚለማበትን ዘዴ እያጠናና በአስተዳደር ጉባኤ እያስወሰነ በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በቋሚ ሲኖዶስ በኩል ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል።
4. ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ በትክክል ገቢ መሆኑን በሕጋዊ መንገድ ወጭ እየሆነ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋሉን ይቆጣጠራል።
5. የየዓመቱን የሥራ ፍሬና የወደፊቱንም ዕቅድ የሚያስረዳ ሪፖርት በየዓመቱ በጥቅምት ወር ለሚደረገው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያቀርባል አጠቃላይ ጉባኤ የመከረበትና ያሳለፈው የውሳኔ ሐሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ሲጸድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።
6. የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓመታዊ በጀት ከታች እስከ ላይ እንዲጠና እያደረገ በዚህ ሕግ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 6 ድንጋጌ መሠረት በቋሚ ሲኖዶስ በኩል ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ቀርቦ ከተፈቀደ በኋላ በሥራ ላይ ያውላል።
7. የቤተ ክርስቲያንዋን እምነትና ሥርዓት ይጠብቃል ፣ ያስጠብቃል።

8. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በቋሚ ሲኖዶስ እያስወሰነ ቤተክርስቲያኒቱን ወክሎ ውል ይዋዋላል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ይከሳል ይከሰሳል።
9. ሥልጣነ ክህነት፣ በቂ የትምህርት ደረጃና ችሎታ ያላቸውን ሦስት ሰዎች ለም/ሥራ አስኪያጅነት በእጩነት ለቋሚ ሲኖዶስ አቅርቦ ያስመርጣል፣በምርጫውም ቅዱስ ሲኖዶስ ሲስማማበት የተመረጠው ሰው በፓትርያርኩ ይሾማል፣የሚጻፍለት ደብዳቤም በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የሚፈረም ሆኖ በፓትርያርኩ ፊቃድ እንደተሾመ ይገለጻል።
10. የመምሪያና የልዩ ልዩ ድርጅት ኃላፊዎችን እያጠናና እየመረጠ ፓትርያርኩን በማስፈቀድ የሾማል።
11. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ኃላፊዎች የሥራ ዝውውርና ዕድገት በተመለከተም በአስተዳደር ጉባኤው እየተጠናና እየተወሰነ እንዲፈፀም የደርጋል።
12. በጠቅላይ ጽ/ቤቱና በየድርጅቱ ያለውን የሠራተኛ ቅጥር፣ ዝውውርና ዕድገት ሁለ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል እያስጠናና ከቤተ ክርስቲያኒቱ የሚወጡትን ደንቦች በመከተል ይፈጽማል፣ያስፈጽማል።
13. በየደረጃው ያለውን የሠራተኛ መብትና ግዴታ በሚመለከት ማለትም የጡረታ፣የጤና አጠባበቅ፣ የደረጃ ዕድገት፣ የፊቃድ አሰጣጥ፣ የዲሲፒሊን ውሳኔ አፈጻጸምና የመሳሰሉትን ሁሉ በዚህ ሕግና በሚወጡት መመሪያዎች መሠረት መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል። አመራርም ይሰጣል።
14. በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ተቋቋሙትን የትምህርት ተቅዋማትና የማምረቻ ድርጅቶችን ሁሉ ይመራል ይቆጣጠራል።
15. በበጀት የተመደበውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብና ንብረት በፊርማው ያንቀሳቅሳል።
16. ከመደበኛው በጀት ሌላ ድንገተ ወጭ በሚያስፈልግበት ጊዜ በቋሚ ሲኖዶስ እያስወሰነ ከመጠባበቂያው በጀት ላይ ውጭ በማድረግ በሥራ ላይ ያውላል።
17. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሥር በሚገኝ በኮሚሽን ወይም በመምሪያ ወይም በድርጅት በት/ቤት ወይም በሌላ የሥራ ዘርፍ ስም የተከፈቱትንና የሚከፈቱትን የባንክ ሒሳቦች በቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና ባንኩ በስሙ ከተከፈተለት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ከሁለቱ ከአንደኛው ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል።
18. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የማይፈርምበትና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የማያውቀው በልዩ ልዩ ሥያሜ የተከፈተና የሚከፈት የባንክ ሒሳብ ሕጋዊነት አይኖረውም።
19. ማናቸውም የቤተክርስቲያኒቱ የገንዘብ ገቢና ወጭ በሕጋዊ የሒሳብ አያያዝና ደንብ መሠረት መሠራቱን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል።
20. በየዓመቱና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ በሕጋዊ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል።

21. በውጭ ሀገር የሚገኙትን አህጉረ ስብከትና አብያተ ክርስቲያናት የሥራ ሂደታቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል።

ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጅ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣

1. ከቅዱስ ሲኖዶስ በመመሪያ ተወስኖ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል።
2. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ወክሎት ይሠራል። የሥራ ድርሻውም በውሰጠ ደንብ ተዘጋጅቶ በቋሚ ሲኖዶስ ጸድቆ ይሰጠዋል።
3. ምክትል ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት አስተዳደር ጉባኤ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት የመምሪያ ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት ማናቸውም አስተዳደር ነክ ጉዳዮች ሁሉ ማየትና መወሰን የሚችል ጉባኤ ነው።
2. የአስተዳደር ጉባኤው ሰብሳቢ የጠቅለይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ነው።
3. የአስተዳደር ጉባኤ ዋና ዋና ተግባራት፣

   ሀ/ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰኑትን ደንቦች፣ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ውሳኔዎች በሥራ እንዲተረጎሙ ያደርጋል።

   ለ/ ከየአንዳንዱ የሥራ ዘርፍ በሚቀርበው ጉዳይ ላይ እየተወያየና የሥራ አፈጻጸም ስልት እያወጣ ይወስናል።

   ሐ/ የአስተዳደር ችግሮች ሲፈጠሩ /ሲከሰቱ/ እያጠናና እየተወያየ ይወስናል።

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን

1. ይህ ኮሚሽን የቤተ ክርስቲያንዋን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦን በሚመለከት የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ነው።
2. ኮሚሽኑ በቦርድ ይተዳደራል።
3. ቦርዱ በቅዱስ ሲኖዶስ ይሰየማል፣ተጠሪነቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ ይሆናል።
4. የኮሚሽኑ ኮሚሽነር በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ በዚህ ሕግ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠት በፓትርያርኩ ይሾማል።
5. ኮሚሽኑ የሚመራው በቦርዱ ተዘጋጅቶና በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በመወጣ ደንብና መመሪያ ይሆናል፣ ተጠሪነቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አህጉረ ስብከት

የሀገረ ስብከት አወቃቀር

1. የሀገረ ስብከት ዋና ጽ/ቤት
2. የሀገረ ስብክት አስተዳደር ጉባኤ
3. የሀገረ ስብከት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች
4. የሀገረ ስብከት ወረዳ ቤተ ክህነት
5. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

የሀገረ ስብከት ዋና ጽ/ቤት

1. የሀገረ ስብከቱ ዋና ጽ/ቤት በሀገረ ስብከቱ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚ ባለሥልጣን ነው።
2. እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ በተሾመ ሊቀ ጳጳስ ወይም ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ይመራል።
3. አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ለሁሉም አህጉረ ስብከት ማዕከል ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ልዩ ደንብና መመሪያ ይተዳደራል።
4. የዋናው ጽ/ቤት የበላይ ተጠሪ መሪ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ነው። ከርሱም ቀጥሎ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ይሆናል።
5. ሀገረ ስብከቱ ዓላማውንና ተግባሩን የሚያስፈጽምባቸው፣ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን የሚያከናውንባቸው ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ይኖሩታል።
6. የሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ጽ/ቤቱ በመስተዳድሩ ርእሰ ከተማ ይሆናል፣
7. የሀገረ ስብከቱ ዋና ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ነው።
8. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አህጉረ ስብከት በሁለት ክፍል ይመደባሉ፣

   ሀ/ በሀገር ውስጥ፡- ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ዳር ድምበር ድረስ ያሉትን፣

   ለ/ በውጭ ሀገር፡- ከቅድስት ሀገር ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በየክፍላተዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአለችበት ቦታ ሁሉ የሚገኙትን ያጠቃልላል።
9. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየጊዜው እየተስፋፋችና የሐዋርያዊ ተልዕኮ እንቅስቃሴዋም እየተጠናከረ በሄደ መጠን ተጨማሪ የሀገር ስብከት ጽ/ቤቶችን ማቋቋም ይቻላል።

የአዲስ አበባ ገረ ስብከት ጽ/ቤት

1. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በዚህ ሕግ በአንቀጽ 35 በንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በሚወጣው ልዩ ደንብ የሚመራ የአስተዳደር ዓቢይ ኮሚቴ የኖረዋል፤ ይህም ኮሚቴ በቅዱስ ሲኖዶስ ይሰየማል።
2. የዓቢይ ኮሚቴው አባላት

   ሀ/ የቅዱስ ሲኖዶስ የሚመረጡ ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ጳጳሳት፣

   ለ/ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ሦስት፣

   ሐ/ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሦስት በድምሩ ዘጠኝ የሆናል።
3. የዓቢይ ኮሚቴው ሰብሳቢ ከቅዱስ ሲኖዶስ ከሚመረጡት ከሦስቱ አባቶች አንዱ ሆኖ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሆናል።
4. የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት የሆናል፣ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ የኮሚቴው አባላት በሙሉም ሆነ በከፊል ለተጨማሪ ሦስት ዓመት ብቻ ሊመረጡ ይችላሉ።
5. ዓቢይ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቋሚ ሲኖዶስ ይሆናል።

የሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሥልጣንና ተግባር

1. የሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ጠቅላላ በሀገረ ስብከቱ ያለውን የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር በኃላፊነት ይመራል።
2. በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙት ገዳማት፣ አድባራት ፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ አባት ነው።
3. የቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የሀገራችንም ፍቅርና አንድነት በሳላም ተጠብቆ እንደኖር እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን እምነት ተከታዮች በተስፋፊ ባዕድ ሃይማኖት እንዳይሰረቁ ብርቱ ጥበቃ ያርጋል።

4. በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 6 እና 7 በተደነገገው መሠረት በሥነ ምግባራቸው የተመሰገኑትንና በትምህርት ደረጃቸው ብቁ የሆኑትን እያጣራ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን የሾማል።
5. በዚህ ሕግ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎችን በሙያቸው ብቁ የሆኑትንና በግብረ ገብነታቸው የታወቁትን እያጠናና እየመረጠ ይሾማል።
6. በሀገር ስበከቱ ውስጥ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት በሚመለከት ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና ከአስተዳደር ጉባኤው ጋር እየመከረ በሀገረ ስብከቱ ከሚገኙት መንግሥታውያንና ሕዝባውያን ድርጅቶች ጋር የጽሑፍም ሆነ የቃል ግንኙነት በማድረግ ሥራውን ያከናውናል።
7. በሀገረ ስብከቱ ያለውን አስተዳደር ጉባኤ በሊቀ መንበርነት ይመራል።
8. ሊቀ ጳጳሱ በትምህርት ችሎታውና በሥራ ልምድ ብቁ የሆነውን እንደሁም ሥልጣነ ክህነት ያለውን የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መርጦ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በማቅረብ ቅዱስ ፓትርያርኩ ሲስማማበት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ፊርማ ይሾማሉ።
9. በሀገረ ስብከቱ ስም በባንክ የሚገኘውን ገንዘብ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል።
10. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙቱን የልዩ ልዩ ክፍል ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን በሀገረ ስበከቱ አስተዳደር ጉባኤ እያስወሰነ ይመድባል፣ አመዳደቡንም ለጠቅላይ ቤተክህነት ያሳውቃል።

<u>የሀገር ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ</u>

1. በዚሁ ሕግ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 8 የተሾመው ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ነው።
2. በየጊዜው በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰኑት መመሪያዎችና ከጠቅላይ ጽ/ቤት የሚተላለፉት ትእዛዞች ሁሉ እንዴት መፈጸም እንዳለባቸው ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ ይፈጽማል ያስፈጽማል።
3. ሊቀ ጳጳሱ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በስብሰባው ላይ በማይገኝበት ጊዜ በሀገረ ስብከቱ ያለውን የአስተዳደር ጉባኤ በሊቀ መንበርነት ይመራል።
4. በበጀት የተመደበውን የሀገረ ስብከቱን ገንዘብና ንብረት ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ ያንቀሳቅሳል።
5. የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ይጠብቃል ያስጠብቃል።
6. ሥራ አስኪያጁ ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ ሳይቀበል ሠራተኛ መቅጠርን፣ ዝውውርን፣ ደመወዝ መጨመርን የመሳሰሉትን ሁሉ መፈጸም አይችልም።
7. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን ሠራተኞች እየተቆጣጠረ ያሠራል።

8. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን የአብየተ ክርስቲያናት የሥራ እንቅስቃሴ በወረዳው ጽ/ቤቶች አማካይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

<u>የሀገረ ስብከት አስተዳደር ጉባኤ</u>

1. የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ በሀገረ ስብከቱ ዋና ጽ/ቤት የሥራ አስፈጻሚ አካል ነው።
2. የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ ነው።
3. የአስተዳደር ጉባኤውን ተግባር በተመለከተም በዚህ ሕግ አንቀጽ 32 ለጠቅላይ ጽ/ቤቱ አስተዳደር ጉባኤ የተደነገገው ለሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤም ተፈጻሚ ይሆናል።
4. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚገኙት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች የአስተዳደር ጉባኤው አባላት ይሆናሉ።

<u>የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት</u>

1. በሀገረ ስብከትና በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚገኝ የሥራ አስፈጻሚ አካል ነው።
2. የወረዳው ቤተ ክህነት ከላይ የሚመጣውን ትእዛዝና መመሪያ ወደታች ከታች ወደላይ የሚመጡትን ጥናቶችና ዕቅዶች ወደላይ ያስተላልፋል።
3. ምእመናን ከክህደትና ከኑፋቄ የሚጠበቁበትን መንገድ ከአብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ጋር እየተመካከረ አስፈላጊውን ይፈጽማል።
4. የሰበካ ጉባኤያትን ያጠናክራል፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ገቢና ወጭ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል።
5. በቃለ ዓዋዲው የተደነገገውን ሁሉ ይፈጽማል ያስፈጽማል።

<u>ስለ አጥቢያ ቤተክርስቲያን</u>

አጥቢያ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚያወጣው ቃለ ዓዋዲ ትመራለች።

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

<u>የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት</u>

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከኦሬንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት፣</u>

ሀ/ ከግብፅ፣

ለ/ ከሶሪያ፣

ሐ/ ከአርመን፣

መ/ ከሕንድ /ማላባር/ ጋር ያላት የነገረ መለኮትና የምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንድነት የተጠበቀ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መብት

1. ያሏትን ጥንታውያን መጻሕፍት እየተረጐመችና በማሳተሚያ ቤቶችዋ እያሳተመች ለተከታዮችዋ ምእመናን አገልግሎት ማዋል ትችላለች።
2. ቤተ ክርስቲያኒቱ በአዋጅ ቁጥር 145/47፣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ 299/57 አንቀጽ 4 እና 354/61 አንቀጽ 4 በሚያዝዘው ድንጋጌ ተጠቅማ ለኅትመት ሥራዋ የሚያስፈልጉአትን ወረቀት፣ቀለም ፣ኘሌት ፣ፊልምና የመሳሰሉትን ጥሬ ዕቃዎች፣ የምትገለገልባቸውን አልባሳትና ንዋያተ ቅድሳት ከውጭ አገር በርዳታና በግዥ ማስመጣት ትችላለች።
3. የቤተ ክርስቲያን መገልገያ አልባሳት፣ መስቀል ጻሕል ጽዋና የመሳሰሉትን ንዋያተ ቅድሳት በራስዋ ኃላፊነት እየሠራችና እያዘጋጀች በአገልግሎት ላይ እንዲውል ታደርጋለች።
4. ቤተክርስቲያናችን ጥንታዊትና ብሔራዊት እንደመሆንዋ ከጥንት ጀምሮ በሊቃውንት ልጆችዋ አማካይነት እየጻፉችና እያዘጋጀች ስትገለገልባቸው፣ ስትጠብቃቸውና ስታስተምራቸው የኖሩት በየገዳማቱ፣ በየአድባራቱና በየገጠር አብያተ ክርስቲያናቱ ያሏትን ልዩ ልዩ ቅርሶች ቤተ መዛግብት ሆና በጥንቃቄ ስትጠብቅ እንደኖረች ሁሉ አሁንም በያሉበት በባለቤትነት የመጠበቅና የማስጠበቅ መብት አላት።
5. የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅርና አንድነቱን አጽንቶ የሀገሩን ዳር ድንበር ጠብቆ ነፃነቱን አክብሮ የኖረው ከቀደምት አባቶቹ በወረሰው የግበረ ገብነት፣ የአገር ወዳድነት፣ የሃይማኖት ጽንዓት ስለሆነ የህንኑ ለትውልድ ለማስተላለፍ አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ ትምህርት ትሰጣለች።
6. ያቋቋመቻቸውን ማሠልጠኛዎችና ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቶች በኮሌጅ ደረጃ ማሳደግና እንዲሁም አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ት/ቤቶችን ማቋቋም ትችላለች።
7. ባቋቋመቻቸውን ት/ቤቶች ሃይማኖታዊነና ቀኖናዋን ታስተምራለች፤ በየገዳማቱና እንዲሁም አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ት/ቤቶችን ማቋቋም ትችላለች።
8. ንብረቷንና ይዞታዋን በሕግ ታስከብራለች።
9. የሰንበት ትምህርት ቤቶችንና የበጐ አድራጉት ድርጅቶችን ታቋቁማለች።
10. ሰንበታትንና ሌሎችንም ዐበይት በዓላት ታከብራለች ታስከብራለች።
11. በአዲስ አበባና በየአህጉረ ስብከቱ ስብከተ ወንጌልን ታስፋፋለች።

የቤተክርስቲያን ግዴታ

1. ቤተክርስቲያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረታት በምድር ያለች መንግሥተ እግዚአብሔር እንደመሆኗ መጠን ስለ ሀገርና ስለ ሰላም ትጸልያለች።
2. ሕዝቦች በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት እንዲኖሩና ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲደርሱ በተለይም የድሆች ወገኖች ችግር እንዲቃለል ከበጎ አድራጊዎች ጋር በመተባበር ያልተቆጠበ ጥረት ታደርጋለች።
3. በሰዎች መካከል የሚፈጠር የእርስ በእርስ አለመግባባትና ግጭት እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ጦርነት እንዳይኖር የማስተማርና የማስታረቅ ኃላፊነት አለባት።
4. ሀ/ የሀገር ሰላም፣አንድነትና ዕድገት

   ለ/ የወገን ነፃነትና ብልፅግና

   ሐ/ የሰው ልጆች እኩልነትና ፍትሕ ርትዕ እንዲሰፍን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልዕኮዋን ታከናውናለች።

ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሀብትና ንብረት

1. አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ የግል የሆነ ገንዘብ ቢኖረው ይረዳቸው ለነበሩ ዕጓለ ማውታና ችግረኞች ይሰጣል። /አብጥሊስ 39/
2. ኤጲስ ቆጶሱ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ሲያከናውንባቸው የቆዩት መጻሕፍት አልባሳት፣ አርዌብርት፣መስቀሎች፣መቋሚያዎችና የመሳሰሉት ሁሉ በቤተክርስቲያኒቱ ንብረትንት በስሙ ተመዝግበው በሀገረ ስብከቱ በሙዚየም ይቀመጣሉ።
3. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሊቀ ጳጳስ ወይም ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ፡

   ሀ/ ሲታመም ከአቅሙ በላይ ከሆነ ቤተክርስቲያኒቱ ታሳክመዋለች፣

   ለ/ ባረፈም ጊዜ ዜና ዕረፍቱ በመገናኛ ብዙኃን ይነገራል።

   ሐ/ ሥርዓተ ቀብሩ በቅዱስ ፓትርያርኩና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ይፈጸማል።

   መ/ በየሀገረ ስብከቱም ጸሎተ ፍትሐት ይደረግለታል።

   ሠ/ ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው ሁሉ የሚያስፈልገው የገንዘብ ወጪ ከሀገረ ስብከቱ ግምጃ ቤት ወጪ ይደረጋል። የሀገረ ስብከቱ የገንዘብ አቅም የማይችል መሆኑ ከተረጋገጡ አስፈላጊውን ገንዘብ ከጠቅላይ ቤተክህነት ግምጃ ቤት ወጪ እንዲሆን ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ያዛል።

የቀድሞው ሕግ ስለመሻሻሉ

1. ከአሁን በፊት ሚያዝያ 30 ቀን 1988 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ወጥቶ የነበረው ሕገ ቤተክርስቲያን በዚህ ሕገ ቤተክርስቲያን ተሻሽሏል።
2. ይህን የሚቃረን ሕግና ደንብ ሁሉ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ

1. ይህ ሕግ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ከጸደቀበት ግንቦት 10 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።
2. ሕጉ ወደፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ታይቶና ተጠንቶ ሊሻሻል ይችላል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ

አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 1991 ዓ.ም